# የሙሁሩ ኢ.ሙሁራዊ አስተያየት

አብርሃም ከበደ

በፕሬፌሰር ፀሐይና በፕሬፌሰር ዳንዔል መካከል የኢትዮጵያ ምጣኔ ሀብት ያለበትን ተጨባጭ ሁኔታና የፓሊስ ይዘት አስመልክቶ ኢሳት ቴሌቪዥን በቅርቡ ውይይት አካሂዶ ነበር። ፕሮፌሰር ዳንዔል በሰነዘሯቸው አስተያየቶች ላይ የምለው ባይኖርም፤ የፕሮፌ. ፀሐይ አመለካከት ግን ብዙ የሚያነጋግር፣ ምናልባትም ለእኔ መሰረታዊ የኤኮኖሚ መርህ የመሰሉኝ ኩነቶች በእሳቸው በኩል ሆኖው ባለማግኘቴ፤ ከተቻለ እሳቸው ይበልጥ ቢያብራሩት ወይንም ሌሎች ይህን ውይይት የተከታተሉ አስተያየታቸውን ቢያቀርቡ ይጠቅማል የሚል እምነት አለኝ። ከሁሉ በፊት ኢሳት ይህንን የመሰለ የሙህራኖች አመለካከት የሚያንጸባርቅና ለተመልካችም ግንዛቤ የሚያስጨብጥ ውይይት በማካሄዱ አወያዩን አቶ የኔዓለም ፋሲሊንና ጣቢያውን ለማመስግን እወዳለሁ።

በአጭሩም ቢሆን አስተያዩቴን ለመስጠት የምሞክረው ፕሮፌ. ፀሐይ ባቀረቡት አስተያየትና ባለቸውም አመለካከት ሲሆን፤ በዚህም የኢትዮጵያ መንግሥት በፋይናንስ ተቋማት ላይ ያለውን አቋም፣ በኢንቬስትመንት ስም ስለሚፈጸመው የመሬት ነጠቃ፣ የመሬት ፖሊስን በተመለከተ ያለውን እውነታ፣ የአባይ መገደብ (የህዳሴ ግድብ)፤ በከተሞች ውስጥ የሚታየውን የሕንጻና የመንገድ ግንባታ በሕዝቡና በአገሪቱ ኤኮኖሚ ላይ ያለውን እንድምታ ባለኝ ግንዛቤ ለመግለጽ ስሞክር፤ ይብዛም ይነስም ሁለቱም ምሁራን ውይይታቸው በእነዚሁ ጉዳዮች ዙሪያ እንደነበር በመግለጽ ነው።

የቴሌኮሚኒኬሽን መሥሪያቤትና የንግድ ባንክን ተቋም መንግሥት ለግሉ ክፍለ ኤኮኖሚ ለመስጠት ያልፈለገበት ዋናው ምክንያት ለሕዝቡ በማሰብና ፍላጎቱን ለመጠበቅ እንዳልሆነ በዚሁ ጉዳይ ላይ ታላላቆቹ የመንግሥታ ባለሥልጣናት የተናገሩት ምስክር ነው። ከጥቂት ዓመታት በፊት አንድ የአገሪቱ ትልቅ ባለሥልጣን የቴሌን ወደግሉ ባለቤትነት መዛወር በተመለከተ ከተናገሩት፤ ‹የምትታለበውን ላም አሳልፈን አንሰጥም› ማለታቸው፤ መንግሥት ሳይቋረጥ የሚያገኘው ጥቅም አንደኛው ምክንያት ሲሆን፤ ሌላው የሕዝቡን እንቅስቃሴ ለመቆጣጠርና የመረጃ ፍሰቶችን ለመገደብ የወሰደው እርምጃ እንደሆነ በተከሰሱት ጋዜጠኞችና በሌሎችም ላይ በመስረጃነት የሚቀርቡት ማረጋገጫ ይሆናሉ። እዚህ ላይ ለክስ የቀረቡት

በስልክም ሆነ በሌሎች መገናኛ ዘዴዎች ያደረጓቸው የጽሑፍም ሆነ የቃል ልውውጦች ለክስ ያበቃሉ ለማለት እንዳልሆነ ግንዛቤ እንዲጨብጥልኝ እጠይቃለሁ፡፡

በባንክ በኩል ያለውን ስንመለከት ደግሞ፤ መንግሥታዊ የሆኑ ድርጅቶች የባንክ አገልግሎት ለማገኘት የሚችሉት ከኢትዮጵያ ባንክ ብቻ እንደሆነ ባልተጻፈ ሕግ በመመራታቸው፤ ሌሎቹ ማለትም የግል ባንኮች ከዚሁ መንግሥታዊ ባንክ የተረፈውን ከመለቃቀም በስተቀር ሙሉ ለሙሉ በሥራው ለመወዳደርበሩ ክፍት አይደለም፡፡ ለዚሁም አንድ ምሳሌ ለማቅረብ፥ በቅርቡ መንግሥት ለኮንደሚንዬም ለመመዝገብ የሚፈልጉ የባንክ ደብተር (አካውንት) የሚከፍቱት በኢትዮጵያ ንግድ ባንክ ብቻ መሆኑን በመግለጹ፤ ለወራት ያህል የዚሁ ባንክ ቅርንጫፎች በራፍ ላይ የነበረው ረጂም ሰልፍ ለዚሁ አባባል ምስክር ነው፡፡

በአባይ መገደብ (የህዳሴው ግድብ)፣ በባቡር መስመር መዘርጋት፣ በፎቆችና በመንገዶች መገንባት ቅር የሚለው ኢትዮጵያዊ አለ ብዬ አላምንም፡፡ እዚህ ላይ መስማማቱና የሀሳብ ልዩነት የሚከሰተው በሥራዎች ቅደም ተከተል ወይንም አስፈላጊነት ወይንም ሌላ አማራጭ ሊኖር አይችልም? በሚለው ጥያቄ ላይ ይሆናል፡፡ ይህንኑ ጉዳይ በምሳሌ ለማብራራት ያህል፤ በረሀብ የተጠቃ ሰው ገንዘብ ሲያገኝ የመጀመሪያ ምርጫው ረሀቡን የሚያስታግስበት ምግብ የማግኘት ጉዳይ እንጂ፤ በዲዛይነር የተዘጋጀ ልብስ ማማረጥ አይሆንም፡፡ በዚህ ላይ ተጨማሪ ማብራሪያ መስጠት አስፈላጊ ስላልመሰለኝ፤ በአጭሩ በአገራችን የሚከናወኑትን የተጠቀሱትን ሥራዎች በሙያው የሰለጠኑና ልምዱም ያላቸው (በተለይም በከተማ እቅድ አወጣጥ ላይ) ባለሙያዎችና ሕዝቡም መክሮበት መከናወን አለበት ለማለት ነው፡፡ የአባይን ግድብ (የህዳሴውን ግድብ) ጉዳይ እንዲያው እንደ አንድ ተራ ዜጋ ስመለከተው፤ ይህ ፕሬጀክት 8 ቢልዮን የአሜሪካን ዶላር እንደሚፈጅ ተነግሯል፡፡ ይህ ገንዘብ እንደ ኢትዮጵያ በመሰለ ደሀ አገር በጣም ብዙ የሚባሉ ብዙ ፕሮጀክቶችን ሊያቋቁም የሚችል እንደሆነ መገንዘብ ይቻላል፡፡ ይህንን ከማድረግ በፊት ሌሎች የኃይል ማመንጫዎች እንደ ተከዜ፣ ግልገል ግቤ፣ ፊንጫና የመሳሰሉት በሙሉ ኃይላቸው እንዲሰሩ ቢደረግ የአገሪቱን የኃይል ፍላጎት ሊያሟሉ አይችሉም?፡፡ ይህን ለጥያቄ አቀረብኩ እንጂ ይበቃሉ አይበቁም ለማለት በቂ መረጃ የለኝም፡፡ ይህ ለመሆን ከቻለ የሚጠይቀው የገንዘብ መጠን እጅግ አንስተኛ ስለሚሆን በተረፈው ሌሎች ሥራዎችን ማከናወን ይቻላል፡፡ ይሄ በፖሊሲ ቀረጻ ላይ የኤኮኖሚክስ ሀ ሁ በመሆኑ፤ በዚሁ ጉዳይ ላይ ሌላ ፖለቲካዊ ምክንያት ሊኖር ይችላል ለሚሉ በቂ መንደርደሪያ ነው፡፡

በአዲስ አበባ የባቡር መስመር ዝርጋታን በተመለከተ፤ ፕሮጀክቱ ከከተማው አቀማመጥ አንጻር ከሚኖረው ከፍተኛ ወጪ በተጨማሪ፤ በዚሁ ምክንያት የፈረሱት ቤቶችና መንገዶች በሙስና ምክንያት የሚከሰተውን ወጪ ጨምሮ የጠየቀውና የሚጠይቀው መዋዕለ ንዋይ እጅግ ከፍተኛ መሆኑ አጠያያቂ አይደለም። እንግዲህ ይህ ተግባራዊ ከመደረጉ በፊት አስፈላጊው ጥናት ተካሂዶል ወይ? የሚለው ጥያቄ አግባብነት ያለው ሆኖ ይገኛል። ለምሳሌ ከተማውን እንዲህ ምስቅልቅል ከማድረግ በፊት ‹አሮጌው አዲስ አበባ› እና ‹አዲሱ አዲስ አበባ› በሚሉ አሰራሮች ከተማውን መቀየስ አይቻልም ነበር?

በሁለቱ ፕሬፌሰሮች ውይይት ከአደረጉባቸው ርዕሶች አንዱ የመሬት ፖሊስና የመሬት ነጠቃ ጉዳይ ነው። በሁሉም የእድገት አመላካች መስፍርቶች እንደሚገለጸውና እንደሚታወቀውም፤ እርሻ የኢትዮጵያ ዋናው የኤኮኖሚ የጀርባ አጥንት እንደሆነ እሙን ነው። ለአጠቃላይ የአገሪቱ ምርት፣ በሥራ ባጠመደው የሰው ብዛት፣ ለአገር ውስጥም ፍጆታም ሆነ ለውጭ ምንዛሪ ግኝት ያለው አስተዋጽኦ ይህንኑ የኤኮኖሚ ዘርፍ በሚመለከቱ እቅዶችና ፖሊሲዎች ላይ ከፍተኛ ጥንቃቄ እንደሚያስፈልግ የሚታመን ነው። የዚህ ጹሁፍ አቅራቢ፤ በአገሪቱ የተለያዩ ክፍሎች በመዘዋወር ከገበሬው ጋር በቅርብ ለመስራትና ለመወያየት እድሉን አግኝቻለሁ። እኤአ በ1999/2000 የኢትዮጵያ ኤኮኖሚ ማኅበር በአደረገው ጥናት መሰረትም የአገሪቱን የእርሻ ምርት ለማሳደግ አንዱና ዋናው አራሹ ገበሬ በመሬቱ ላይ የባለቤትነት ስሜት እንዲኖረው ማድረግ ነው። በተከታይ የቀረቡ ብዙ ጥናቶችም ይህንን ያረጋግጣሉ። ከእነዚህም አንዱ፤ በቅርቡ ለንባብ ባበቁትና ‹ይድረስ ለግንቦት፥ ከየካቲት› በተሰኘው ርዕስ አቶ ነገደ ጎበዜ በ2006 ዓ.ም ባቀረቡት መጽሐፍ ‹ዛሬ በተቃዋሚ ጎራ እስከዚህም ትኩረት ባይሰጠውም፤ መሬት ላራሹ የሚለው መፈክር ለሀገራችን ገበሬዎች ከፊውዳሉ ዘመን በአላነሰ መልክ አንገብጋቢ የሆነ የትግል መፈክር ነው› በማለት ይህንኑ የመሬት ባለቤትነት ጉዳይ ገልጸውታል። በአጭሩ፤ ገበሬው በመሬቱ ላይ ሙሉ ዋስትና ቢኖረው፣ የመንግሥት ጣልቃ ገብነት በማዳበሪያ አጠቃቀምና በሌሎችም ባይጫንበት የአገራችን አጠቃላይ የእርሻ ምርት ውጤት ከፍተኛ እምርታ ሊያሳይ እንደሚችል እምነት አለኝ። የቀድሞው ጠቅላይ ሚኒስትር ስለዚሁ የመሬት ባለቤትነት ጉዳይ አንስተው ሲናገሩ፤ ‹መሬት የሚሸጠውና የሚለወጠው በኢሕአዴግ መቃብር ላይ ነው› ብለው መናገራቸው የሚታወስ ነው። ለዚህም አባባላቸው በእኔ እምነት ሁለት ምክንያቶች አሏቸው። በነገራችን ላይ፤ ድርጅታቸው የሚወስዳቸው እርምጃዎች በአብዛኛው

ከአንድ በላይ ዓላማ ይዘው እንደመሆኑ፤ በዚህም የመሬት ጉዳይ የፖለቲካ የበላይነቱን ለማረጋገጥና ለውጭ ባለሀብቶች በመሸጥ ድርጅታቸው የፍይናንስ አቅሙን ለማጎልበት እንደሆነ አሰራሩ ይመሰክራል፡፡

‹በኢንቪስትመንት ስም የሚፈጸም የመሬት ነጠቃ በኢትዮጵያ› በሚል ርዕስ፤ የኦክላንድ ተቋም እና ለአዲሲቱ ኢትዮጵያ ንቅናቄ የተባሉ ድርጅቶች በጋራ ያቀረቡት ጠቃሚ ጥናት፤ በዚሁ ዓብይ ጉዳይ ላይ ግንዛቤ ለማግኘት ለሚፈልጉ ኢትዮጵያዊያን (ፕሬፌ. ፀሐይን ጨምሮ) ቢነበብ ይጠቅማል የሚል አስተያየት አለኝ፡፡ በዚሁ ጉዳይ በኢትዮጵያ ያለውን ተጨባጭ ሁኔታ ስንመለከት ይህ የመሬት ለውጭ ‹ኢንቬስተሮች› በኪራይ መልክ መስጠት ለኢትዮጵያ ሕዝብ የሚሰጠው ጥቅም የሌለ ብቻ ሳይሆን ጉዳቱ የሚያመዝን መሆኑን በሚከተሉት አራት ነጥቦች ላብራራ፥

1. በመሬት ነጠቃው ምክንያት በአካባቢው ይኖሩ የነበሩ ገበሬዎችና ሌሎች ነዋሪዎችም እስከነቤተሰባቸው ይፈናቀላሉ፡፡ የነዋሪዎቹም ማኅበራዊ ትስስርና እሴታቸውም ይዛባል፡፡
2. አገራዊ ስሜት በሌላቸው የውጭ ‹ኢንቬስተሮች› በሄክታር የሚያገኙትን የምርት መጠን ለመጨመር በመሬቱ ላይ የሚያፈሱት ገደብ የለሽ ኬሚካል፤ የመሬቱን ለምንት በተፋጠነ ሁኔታ ከመቀነሱ በላይ የአካባቢውንም ገጽታ ያበላሻዋል፡፡
3. የኢንቪስተሮቹ አስተራረስና አመራረት በዘመናዊ የማረሻና የመውቂያ ዘዴ በመሆኑ ለአካባቢው ሕዝብ የሚፈጥሩት የሥራ እድል፤ ከመሸከምና ከማውረድ ያላለፈ ከመሆኑም በላይ የተፈናቀሉት ገበሬዎች ተጨማሪ ችሎታቸውን (skill) የሚያዳብሩበት እድል የለም፡፡
4. የሚመረተው ምርት ወደ አገራቸው የሚላክ በመሆኑ ከአሀዝ ባለፈ አገሪቱ በውጭ ምንዛሪም ሆነ በምግብ አቅርቦት መጨመረ የምታገኘው ጥቅም አይኖርም፡፡

ከዚህ በላይ በተወሰኑ ነጥቦች ለመግለጽ እንደተሞከረው የመሬት ነጠቃው የሚያስከትለው ጉዳት ይበልጥ አመዝኖ ይገኛል፡፡ በተለይ የአበባን ምርት ስንመለከት ደግሞ ያለው ገጽታ እጅግ የከፋ ሆኖ እናገኘዋለን፡፡ በአበባ አመራረት የሚታወቁ አገሮች የዚህን አሰራር ጉዳት በመገንዘብ ከሥራው እያፈገፈጉ ይገኛሉ፡፡ ‹ከሞኝ ደጃፍ . . .› እንደሚባለው፤ እኛ ግን እጃችን ዘርግተን የምንቀበላቸውን እነኚህኑ የውጭ ኢንቬስተሮች፤ በወሰዱት የመሬት ብዛትና ሊያመርቱ

የሚችሉትን እንዲሁም ለገበያ ያቀረቡትን እንደ ትልቅ ውጤት በመቁጠር ስንናገር እንሰማለን፡፡ ይህን የሚያንገበግብና የሚያስቆጭ ድሪጊት በአጭሩ ላብራራ፡፡

ኢትቪስተሮች ወይንም አምራቾች ምርቱን በብዛትና በአጭር ጊዜ አምርቶ ለገበያ ለማቅረብ በሚያደርጉት ጥረት ከአንድ ወር ባነሰ ጊዜ ያደርሱታል፡፡ ቀደም ሲል እንደተገለጸው ሁሉ፤ ይህንን ለማከናወን የሚጠቀሙበት ኬሚካል የመሬቱን ለምነት ለብዙ ዓመታት የሚያጠፋ ከመሆኑ በተጨማሪ በሥራው ላይ የተሰማሩትን ሠራተኞች ጤንነት የሚጎዳ ነው፡፡ በተለይ በአበባ ሥራ ላይ በብዛት የተሰማሩት ሴቶች እንደመሆኑ፤ የሚያስከትለው የጤንነት ጉዳት እነኝህኑ ሴቶች መሆን እስከመሆን የሚያደርስ ነው፡፡ የውጭ ኢንቬስተር አምራቾች ሥራውን ሲጀምሩ ከመንግሥት ጋር በሚያደርጉት ስምምነት መሰረት፤ ሠራተኞችን ቢያንስ በየስድስት ወሮች ጤንነታቸውን ለማስመርመርና በተጨማሪም በሥራ ላይ እያሉ ወተት የማቅረብ ግዴታ ገብተዋል፡፡ ሆኖም ይህንን ስምምነት ተግባራዊ ለማድረግ በቂ ክትትል የሌለ ሲሆን፤ ሠራተኞቹም በዚህ በኩል ያላቸውን መብት የማወቅ ግንዛቤ የሌላቸው መሆኑን ቀርቦ ለሚያነጋግራቸው መገንዘብ ይቻላል፡፡

አበባም ሆነ ሌሎች የቆይታ ጊዚያቸው በጣም አጭር (perishable) የሆኑ ምርቶች ለውጭ ገበያ የሚሸጡት በአደራ ሽያጭ (consignment) ነው፡፡ ይህ የአሻሻጥ ስልት ላኪም ተቀባይም የአንድ ኩባንያ ባለቤቶች በሆኑበት (በኢትዮጵያ አምራቾችና ተቀባዮች ይዘት ይህ በብዛት የሚታይ ነው)፡፡ ለምዝበራ የተጋለጠ ለመሆኑ አያጠራጥርም፡፡ በዚህ በኩል ከኢትዮጵያዊያን ሽሪኮቻቸው ጋር በጋራ የሚሰሩ የውጭ ዜጎች ያደረሱትን ማጭበርበርና ኪሳራ በቀላሉ የሚገመት አይደለም፡፡

ፕሮፌ. ፀሐይ በኢትዮጵያ በአደረጉት ጉብኝት ለአንድ ወዳጃቸው ከሁለት ዓመት በኋላ ጠቅልለው እንደሚመጡ ሲገልጹለት የሰጣቸው አስተያየት እንዲህ በማለት ነበር፥ ‹ጋሼ! ያኔ አዲስ አበባ የምትቀየር በመሆኑ አታውቃትም› ያላቸው ሲሆን፤ ይህንንም ለማለት ያስቻለው፤ በሚሰረቱ ፎቆች፣ በመንገድ ግንባታውና በሚፈናቀሉት ወገኖች ምክንያት መሆኑ ነው፡፡ በእርግጥም የተፈለገውና የሚሰራውም ይህንኑ በተግባር ለማዋል እንደሆነ ግልጽ ነው፡፡ እሳቸውም ሊጠይቁ የሚገባው ሕዝቡ እየተፈናቀለ የሚሰሩት ፎቆች በማን፣ለማና ከየት በተገኘ

ገንዘብ እንደሆኑና የሚዘረጉት መንገዶችም ከጀርባቸው ያለውን ትውልድ ሊወጣው የማይችል እዳና ያለውን ሙስና ማወቁ ላይ ነው፡፡

በመጨረሻም! ከከፍተኛ አክብሮት ጋር ለፕሮፌሰሩ ያለኝን አስተያየት ለማቅረብ እወዳለሁ፡፡ በተጠቀሰው ቃለ መጠይቅና ውይይት ላይ ያቀረቡት ሀሳብ መሰረት ያደረገው በጭፍን ወገናዊነት ከሆነ እንኳን አገርን ለሚመራ አካል ቀርቶ ለግለሰብም ቢሆን፤ ከእውነታው ያፈነገጠ አስተያየት መስጠት ጠቃሚ አይደለም፡፡ በሌላ በኩል በመሬት ላይ የሚታየውን ተጨባጭ እውነታ ባለማወቅ የተሰነዘረ ከሆነ፤ ባለዎት ሙሁራዊ ችሎታ የበለጠ ምርምር በማድረግ አመለካከተዎን እንደገና ቢመረምሩና ግኝትዎንም ቢያካፍሉነት መልካም ነው እላለሁ፡፡